# ወዶ ገብ

ኢትዮጵያ ተርፏታል _ በዕውቅ የተሰራ ሰው
ባለቤቱ እንዳሻው _ ቆዳ የሚያለብሰው
ሲሻው ያቀልመዋል _ ህዝቡን አስመስሎ
አለያም ምላሱን _ አንደበቱን ስሎ
ወይንም በሥራው _ ግብሩን ተከትሎ
ጥቅሙን እንዲያስጠብቅ _ አቤት ወዴት ብሎ
ቆዳውን ገለብጦ _ መልበሱ እንዳይጎላ
ዘዴ ተዘይዶ _ ተፈልጎ መላ
መስፍኑ እንደ መስፍን_ ያቀቡ እንደ ያቆብ
ሀይሉው እንደ ሀይሉ_ ለመሪነት ሲቀርብ
ጭንብሉን አጥልቆ _ መድረክ ላይ ሲዋነብ
እንደዬ ተልዕኮው _ ታጥፎ ሲዘረጋ
ተዋናኝ ሲመስል _ የት የሌለ ዜጋ
የጓህ ልብ አይልም _ ተውኔቱ እስኪዘጋ።

አስመሳይ በሽንጎ _ ወዶገብ ሆድ አደር
ማግኘት ምን ቸግሮ _ ከሼህ እስከ ዶክተር
ከዲያቆን እስከ አቡን _ ውስጥና ውጭ አገር
ሰው አለ ባይነቱ _ምን ገዶ እበላ ባይ
የበግ ለምድ ለብሶ _ የተኩላ ሰላይ

እኛን የቸገረን _ የነቃ የበቃ
የማይቸረቸር _ እንደ ሸቀጥ ዕቃ
ህዝብ ያለመኖር ነው _ አስተዋይ ጠንቃቃ።

ግንቦት 2001

abraham beyenne